Amharic

# በዩናይትድ ኪንግደም በሰላም ስለመኖር

## ጥገኝነት ለሚጠይቁ ልጆችና ወጣቶች የሚሆን በወሲባዊ በደልና ወሲባዊ ጥቃት ላይ ያተኮረ የመርጃ ሰብስብ

## አርዕስት ማውጫ


የዚህ የመረጃ ስብስብ አላማ ምንድነው? ይህንን የመረጃ ስብስብ ማንበብ ያለበትስ ማን ነው? ...... 2
ወሲባዊ በደል ወይም ወሲባዊ ጥቃት ሲባል ምን ማለት ነው? .................................................... 3
ወሲብን፡ ወሲባዊ በደልንና ጥቃትን በሚመለከት የብሪታኒያ ህግ ምን ይላል? ................................ 3
ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ሊፈፅሙባችሁ የሚችሉት እነማን ሊሆኑ ይችላሉ? .............................. 4
ለወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ልትጋለጡ የምትችሉበት ሁኔታ ምንድነው? ............... ............ 4
ለወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት መጋለጣችሁን እንዴት ማወቅ ትችላላችሁ? .............................. 5
ለወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት መጋለጣችሁን ከተረዳችሁ ምን ማድረግ ይኖርባችሃል? .................. 5
ከአሁን ቀደም ያጋጠማችሁ ነገር ካለ ወይም ወደፊት ቢያጋጥማችሁስ? ................................... 6
ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ከተፈፀመባችሁ የሕክምና ዕርዳታ ለማግኘት ትሞክራላችሁ? ............ 6
ሁኔታውንስ ለፖሊስ ብታሳውቁ ምን ሊፈጠር ይችል ይሆን? ............................................... 7
ስለ ሁኔታው ለማንም ሰው መንገር ከፈራችሁ ምን ማድረግ ትሞክራላችሁ? .............................. 7
ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት የሚያሳስባችሁ ከሆነ ሊረዳችሁ የሚችሉ ሰዎች መረጃ ............... 8

## የዚህ መረጃ ስብስብ ዓላማ ምንድነው? ይህንን የመረጃ ስብስብ ማንበብ ያለበትስ ማን ነው?

ይህ የመረጃ ስብስብ ወደ ብሪታኒያ ጥገኝነት ጠይቀው የመጡ ልጆችንና ወጣቶችን በተለይም ወላጅ ወይም ሌላ የሚንከባከባቸው አዋቂ ሰው ሳይኖር ብቻቸውን እንግሊዝ ሀገር የገቡ ልጆችንና ወጣቶችን ለመርዳት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የመረጃ ስብስቡ ለልጆችና ዕድሜያቸው ከ11 ዓመት በላይ ለሆኑ ወጣቶች የተዘጋጀ ነው።

በመጀመሪያ እንኳን በደህና ወደ ብሪታኒያ መጣችሁ። በአገራችሁ ተረጋግታችሁ መኖር አለመቻላችሁ በጣም ያሳዝናል። ምንም እንኳን አገራችሁ ውስጥ ኑሮው ከባድ ሊሆን ቢችልም መነሻ ላይ ራስን ከዚህ ሀገር ኑሮ ጋር ማለማመድ ደግሞ አስቸጋሪ ሆኖ ልታገኙት ትችላላችሁ። እንግሊዝኛ ቅንቅንና የእንግሊዛውያንን አናናር ዘዴ መማር ይኖርባችሁዋል። ከዚህ በተጨማሪ አዲስ እንደመሆናችሁ መጠን እዚህ ሀገር ሊያጋጥማችሁ ስለሚችሉ ችግሮችም ሆነ ልታገኙት ስለሚገባ ርዳታ አታውቁም ይሆናል።

አብዛኞቹ እዚህ አንግሊዝ ውስጥ የምትገናኛቸው ሰዎች ጥሩና ደግ ሊሆኑ ስለሚችሉ እምነት ልትጥሉባቸው ትችላላችሁ።ነገር ግን በየትኛውም የዓለም ክፍል እንዳለው ሁሉ እዚህም መጥፎ ነገር የሚያደርጉ ሰዎች አሉ። በተለይ ወሲባዊ በደል ወይም ወሲባዊ ጥቃት ሊፈፅሙባችሁ የሚፈልጉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ ምን ማለት እንደሆነ እዚህ ፅሁፍ ውስጥ ተብራርቶ ታገኙታላችሁ። ፅሁፉ ለወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ይበልጥ ሊያጋልጣችሁ ስለሚችሉ ነገሮች የሚያብራራ ሲሆን ሁኔታው እንዳይፈጠር ለማድረግም ከየትኛው ወገን ርዳታ ማግኘት እንደምትችሉ ይገልጽላችሃል። አጋጣሚ ሆኖ ከተፈጠረም ምን ዓይነት ርምጃ መውሰድ እንዳለባችሁ ያመለክታችሃል። ዓላማውም አንባቢዎችን ለማስጨነቅ ሳይሆን ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ አደጋዎችና ርዳታ ሊያድርጉ ስለሚችሉ ሰዎች ማወቁ ይጠቅማል የሚል ነው

## ወሲባዊ በደል ወይም ወሲባዊ ጥቃት ሲባል ምን ማለት ነው?

ወሲባዊ በደል ማለት አንድ ሰው ሌላኛው ሰው ሳይፈልግ ወይም ምን እየተደረገ እንኳን ሳያውቅ በግለሰቡ ላይ የሚፈጽመው ወሲባዊ ድርጊት ነው። ድርጊቱ የአንድን ሰው አካል ወይም ሌላ ሰው ሊነካቸው የማይገቡ የሰውነት ክፍሎችን ወሲባዊ በሆነ መንገድ መነካካትን ወይም ወሲባዊ ፊልም ማሳየትን ይጨምራል። አንዳንድ ወሲባዊ በደል ፈፃሚ ሰዎች ልጆችንና ወጣቶችን ወሲባዊ ድርጊት እንዲፈጽሙላቸው ለማግባባት ሲሉ ስጦታዎች ወይም ማባበያዎች ይሰጣቸዋል።ወሲባዊ ጥቃት አስገድዶ መድፈርንና አብዛኛውን ጊዜ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ የሚፈጸሙ ሌሎችንም ወሲባዊ ድርጊቶችንም ይጨምራል። እንደነዚህ ያሉ ሁኔታዎች እናንተ ላይ ደርሰውባችሁ ወይም በምታውቋቸው ሰዎች ላይ ተፈፅሞ ሊሆን ይችላል። የሚያሳዝነው እዚህ ሀገር ሁኔታው በወንዶች እንዲሁም በሴቶች ልጆች ላይ ሊፈፀም መቻሉ ነው። ወሲባዊ በደልና ወሲባዊ ጥቃት በልጆችና በወጣቶች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። ከእንደዚህ ዓይነቱ ጉዳት የመጠበቅ መብት አላችሁ።.

## ወሲብን፣ ወሲባዊ በደልንና ጥቃትን በሚመለከት የብሪታኒያ ህግ ምን ይላል?

እዚህ ብሪታኒያ ውስጥ ዕድሜያቸው 16 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑና ሁለቱም በተስማሙበት ሁኔታ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ጾታ ካላቸው ሰዎች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም እንደሚቻል ህጉ ይደነግጋል። አዋቂዎች ከ 16 ዓመት በታች (በሰሜን አየርላንድ 17 ዓመት ነው) በሆኑ ልጆች ላይ ከወሲብ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ድርጊት ከፈጸሙ ህገ-ወጥ ተግባር ይሆናል። ይህም መነካካትን የማይጨምሩ ነገሮችንም ያጠቃልላል። በተጨማሪም ከልጆች ጋር የሚሰሩ ሰዎች ለምሳሌ ያህል አስተማሪዎች ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች ከሆኑና በእነርሱ እንክብካቤ ስር ካሉ ልጆች ጋር ከወሲብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ከፈጸሙ ህገ-ወጥ ተግባር ይሆናል። **በየትኛውም የዕድሜ ክልል ሁኑ፣ ጠያቂው ማንም ይሁን ማን ወሲባዊ ድርጊቶች እንድትፈጽሙ ለሚቀርብላችሁ ጥያቄ ‘እምቢ’ የማለት መብት አላችሁ።**

## ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ሊፈጽሙባችሁ የሚችሉት እነማን ሊሆኑ ይችላሉ?

ምንም እንኳን አብዛኛውን ጊዜ በልጆች ላይ ወሲባዊ በደል የሚያደርሱት ወንዶች ቢሆኑም አንዳንድ ሴቶችም ተመሳሳይ ድርጊት ይፈጽማሉ። እነዚህ ድርጊቱን ፈፃሚዎች ደግሞ የሚመርጡት ከእነርሱ በዕድሜ የሚያንሱ ወይም ደካማ የሆኑ ወንዶች ልጆችን ወይም ልጃገረዶችን ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ የዕድሜ እኩዮቻቸውን ወይም የሚበልጣቸውን ሰዎች ለማጥቃት ይሞክራሉ።አልፎ አልፎም ልጆችን የሚንከባከቡ ወይም ሥራቸው ከልጆች ጋር የሆኑ አዋቂዎች በልጆች ላይ ወሲባዊ በደል ሲፈጽሙ ይገኛሉ። **ምንም እንኳዋን ሁሉም ዓይነት ሰዎች በልጆች ላይ ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት የሚፈጽሙ ቢሆኑም ብዙዎች ግን ይህንን አያደርጉም። እንዲያውም አብዛኞቹ አዋቂዎች እንዲህ ላለው ጥቃት እንደተጋለጣችሁ ካወቁ ጉዳት እንዳይደርስባችሁ ሊከላከሉላችሁ ይፈልጋሉ።**

## ለወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ልትጋለጡ የምትችሉበት ሁኔታ ምንድነው?

በተለይ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ከቤተሰቦቻችሁ በመለየታችሁ ብቸኝነት ሊሰማችሁ ይችላል። በዚህ ምክንያት ብዙ እንክብካቤ፣ ትኩረትና ተግባራዊ ርዳታ ያስፈልጋችሁኣል። እንዲህ ዓይነቱን ዕገዛ ማግኘት የምትፈልጉት ደግሞ የእናንተን የኑሮ ሁኔታና ቋንቋ ከሚያውቁና በዕድሜ ከፍ ካሉ የአገራችሁ ሰዎች ሊሆን ይችላል። ይህ ግን ለወሲባዊ በደል እንድትጋለጥ ሊያደርጋችሁ ይችላል። ወጣትነት፣ ሴትነትና ለብሪታኒያ እንግዳ መሆንም ለዚህ ችግር ሊያጋልጡ ከሚችሉ ነገሮች መካከል ይጠቀሳሉ። በተጨማሪም ለወሲባዊ በደልና ጥቃት የመጋለጥ አደጋ እንዳለ አለመገንዘብ ወይም ከዚህ ጥቃት የመጠበቅ መብትን አለማወቅ ለችግሩ የምትጋለጡበትን አጋጣሚ ከፍ ያደርገዋል። **ስለዚህ ልታምንአቸው እንደምትችሉ አርግጠኛ እስከምትሆኑ ድረስ አዳዲስ ግዋደኞቻችሁን ህዝብ በሚበዛባቸውና ለደህንነታችሁ በማያሰጉ ቦታዎች መቅጠሩ ይመረጣል።**

## ለወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት መጋለጣችሁን እንዴት ማወቅ ትችላላችሁ?

ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው እናንተን የሚያይበት ወይም የሚያስተናግድበት ሁኔታ አያስደስታችሁ ይሆናል። እንደዚሁም በዕደሜ ከእናንተ የሚበልጥ ሰው በጣም ተግባቢ ሆኖ ልታገኙትና ብዙ ሰጦታዎችን ሊሰጣችሁ ወይም ብዙ ጥሩ ነገሮችን ሊያደርግላችሁ ይችል ይሆናል። በቡድን የሆኑ ወንዶች ልጆች ወይም ወጣት ወንዶች በመኖሪያ አከባቢያችሁ ሊሰበሰቡና ከወሲብ ጋር የተያያዙ ነገሮች ሊነግሩአችሁ ወይም እናንተን ለመነካካት ይሞክሩ ይሆናል። አንድ ሰው በእናንተ ላይ ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ለመፈጸም እየሞከረ እንደሆነ ከተሰማችሁ ይህንኑ ስሜታችሁን መከታተል ተገቢ ይሆናል። በኀላ ከማዘን አስቀድሞ መጠንቀቅ ይበጃልና።

## ለወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት መጋለጣችሁን ከተረዳችሁ ምን ማድረግ ይኖርባችሁዋል?

በልጆች ላይ ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት መፈጸም የሚፈልጉ ሰዎች ጉዳይ ምስጢር ሆኖ እንደማይቀር ካወቁ ድርጊቱን ለመፈጸም አይደፍሩም። ለዚህም ነው ለወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት መጋለጣችሁን ከተረዳችሁ ለአንድ ለምታምኑት አዋቂ ሰው መንገሩ አስፈላጊ የሚሆነው። ለምሳሌ ያህል ጉዳዩን ለማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ (ሶሺያል ዎርከር)፣ ቁልፍ ሰራተኛ (ኪይ ዎርከር) አሳዳጊ ወላጅ ወይም አስተማሪ ለመንገር ትችላላችሁ። እነዚህ ሰዎች ጤንነታችሁንና ደህንነታችሁን የሚንከባከቡ ሰዎች ናቸው። ነገር ግን ለእነሱ መንገር እንደማትችሉ ሆኖ ከተሰማችሁ ወይም ከእነርሱ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ጥሩ ካልሆነ ከሌላ ሰው ርዳታ ለማግኘት መጣር ይኖርባችኋል። አዋቂዎች እናንተን ከጥቃት ለመከላከል አንድ ነገር ያደርጋሉና። በዚህ ፅሁፍ መጨረሻ ላይ ርዳታና ድጋፍ ልታገኙ የምትችሉባቸውን አንዳንድ ቦታዎች ዘርዝረናል። ሌሎችም ተጨማሪ ቦታዎች አሉ። **በተሻለ መንገድ ከጥቃት መጠበቅ የምትችሉብትን ሁኔታ እስከሚያመቻቹላችሁ ድረስ ለምታምኑአቸው አዋቂ ሰዎች ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃትን በሚመለከት ያላችሁን ከመንገር አትቆጠቡ።**

## ከአሁን ቀደም ያጋጠማችሁ ነገር ካለ ወይም ወደፊት ቢያጋጥማችሁስ?

እንዲህ ዓይነት ነገር ካጋጠማችሁ ለገደኞቻችሁ ስለሆነው ነገር ብትነግሩት ይቀላችሁ ይሆናል። ሆኖም ጉዋደኞቻችሁ ብዙም ላይረዳችሁ ይችሉ ይሆናል። ለዚህም ነው በተቻለ ፍጥነት ለምታምኑት አዋቂ ሰው ለምሳሌ ለአስተማሪ ወይም ለማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ መንገር የሚያስፈልገው። ሁኔታው በድጋሚ እንዳይከሰት ለማድረግ የሚያስፈልጋችሁን ማንኛውንም ርዳታ እንድታገኙ ሊረዳችሁ ይችላሉ። በተጨማሪም ጉዳዩን ለሚታመን አዋቂ ሰው መንገር ጥቃቱ በሌሎች ልጆች ወይም ወጣቶች ላይ እንዳይደርስ ለመከላከል ይረዳል። **አንድ ሰው በእናንተ ላይ ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ቢያደርስባችሁ ጥፋቱ የእናንተ እንዳልሆነ አስታውሱ። እናንተ ልጆች እንደመሆናችሁ መጠን ጥበቃ የማግኘት መብት አላችሁና።**

## ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ከተፈፀመባችሁ የሕክምና ዕርዳታ ለማግኘት ትሞክራላችሁ?

እንደደረሰባችሁ ጉዳት መጠን የህክምና ርዳታ ያስፈልጋችሁ ይሆናል ወይም ጉዳዩን የምትነግሩት ሰው ማግኘት ይኖርባችሁ ይሆናል። ስለ ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት ለሀኪም ወይም ለነርስ መንገርም ሊከብዳችሁ ይችል ይሆናል። ነገር ግን የሚያስፈልጋችሁን ርዳታና ህክምና ማግኝት እንድትችሉ ምን እንደደረሰባችሁ በትክክል ማወቅ ይኖርባችሁዋል። እንግሊዘኛ በደንብ መናገር የማትችሉ ከሆነ ይህንኑ እንዲያውቁት ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ሀኪም ጋር ስትቀርቡ በቋንቋ ረገድ ያለውን ችግር ለመፍታት ሰው እንዲመደብላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ። ይህ ግለሰብ ለሀኪሙ ወይም ለነርሳ የምትነግሩትን ሁሉ በምስጢር መያዝ ይኖርበታል። **ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት አካላዊ ጉዳቶች ሊያስከትልና በጣም የሚያበሳጭ ሊሆን ይችላል። ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ ብዙ ሳይቆዩ ለሀኪም መንገር ብልህነት ነው።**

## ሁኔታውንስ ለፖሊስ ብታሳውቁ ምን ሊፈጠር ይችል ይሆን?

በማናቸውም ጊዜ ለወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት መጋለጣችሁን ከተረዳችሁ በስልክ ቁጥር 999 በመደወል ለፖሊስ መንገር ወይም ለፖሊስ ጣቢያ ማሳወቅ ትችላላችሁ። ጥበቃ እንድታገኙ ይረዱአችኋል። ድርጊቱ ከተፈጸመ እንኳዋን ትንሽ የቆየ ቢሆንም የደረሰባችሁን ነገር ልትነግሯቸው ይገባል። በመጀመሪያ የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞችሁ ወይም ሌላ የሚታመን አዋቂ ሰው እንዲነግሩላችሁ ትፈልጉ ይሆናል። ፖሊሶችም በደል ወይም ጥቃት የተፈጸመባቸውን ሰዎች ሊረዱ የሚችሉ የተለየ ስልጠና የወሰዱ መኮንኖች አላቸው። በደግነትና በአክብሮት ይይዙአችኋል።ያም ሆኖ ልታምኑት የምትችሉትን ሰው ይዞ መሄድ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ከፈለጋችሁ ከሴት ጠና ባለሙያ ጋር ለመነጋገር መጠየቅ ትችላላችሁ። አስፈላጊም ከሆነ በቋንቋ የሚረዳችሁን ሰው እዚያ ማግኘት ትችላላችሁ። **ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት እንደተፈጸመባችሁ ለፖሊስ (ወይም ለሌላ ለማንኛውም ሰው) መግለጻችሁ በብሪታኒያ መቆየት አለመቆየታችሁ ላይ ምንም ዓይነት ተጽእኖ አያሳድርም።**

## ስለ ሁኔታው ለማንም ሰው መንገር ከፈራችሁ ምን ማድረግ ትሞክራላችሁ?

ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት እንደተፈጸመባችሁ ለሌሎቸ መንገር በጣም ያሳፍራችሁ ይሆናል። ሌሎች ስለእናንተ ሊያስቡ ወይም ሊያደርጉ የሚችሉትን ነገር በመፍራት ወደኋላ ትሉም ይሆናል። ምናልባትም የፈጸመባችሁ ሰው ለማንም እንዳትናገሩ አስጠንቅቆአችሁ ይሆናል። በተጨማሪም ከተናገርን ወደ አገራችን ሊመልሱን ይችላሉ (ምንም እንካን ይህ ኣንድትመለሱ የሚያደርጋችሁ ባይሆንም) ብላችሁ ፈርታችሁ ይሆናል። ከማንም ሰው ጋር ፊት ለፊት መነጋገር ካልፈለጋችሁ ከዚህ በታች በተገለጹት የርዳታ ማግኛ ስልክ ቁጥሮች ወደ አንዱ በመደወል ከአንድ ሰው ጋር በስልክ መነጋገር ትችላላችሁ። ስማችሁን አለመግለጽ የምትችሉ ሲሆን በምስጢር አጠባበቅ ረገድ

የሚመሩባቸው ህጎች ምን እንደሆኑ ጠይቆ መረዳት የተሻለ ይሆናል። ስለ ወሲባዊ በደልና ጥቃት ልታነጋግሯቸው የምትችሉአቸውና ሊረዱችሁ የሚችሉ አዋቂዎች አሉ። ጥበቃ የማግኘት መብት አላችሁ።

## ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት የሚያሳስባችሁ ከሆነ ሊረዱችሁ የሚችሉ ሰዎች መረጃ

የወሲባዊ ጥቃት ሰለባዎች መርጃ ማዕከላት፡- እነዚህ በመላው አገሪቱ የሚገኙና ልጆችን ጨምሮ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች የሚረዱ ማዕከላት ናቸው።። የህክምና ርዳታ፣ የምክር አገልግሎት፣ እንዲሁም ተግባራዊና ስሜታዊ ድጋፍ ይሰጣሉ። አገልግሎታቸውን ለማግኘት የግድ ስለተፈጸመው ድርጊት ለፖሊስ መንገር አያስፈልግም። እንግሊዘኛ መናገር የማትችሉ ከሆነ አንዳንድ ማዕከላት ሊረዱችሁ የሚችሉ አስተርጉአሚዎችን ያዘጋጃሉ።

የምትኖሩት ከለንደን ከተማ ውጭ ከሆነ የሚታመኑና አዋቂ ሰዎችን ማለትም እንደ ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች፣ ጉዳይ ተከታታዮች ወይም ሀኪማችሁን በአከባቢያችሁ ስለሚገኘው የወሲባዊ ጥቃት ሰላባዎች መርጃ ማዕከል (Sexual Assault Referral Centre) ዝርዝር መረጃ እንዲስጧችሁ ጠይቁ። ጉዳያችሁን ሊያስረዱኋችሁ ይችላሉ ወይም ራሳችሁ ቀርባችሁ ታስረዳላችሁ።

የአንዳንዶቹ በለንደን ከተማ የሚገኙ የወሲባዊ ጥቃት ሰለባዎች መርጃ ማዕከላት ዝርዝር የሚከተለው ነው፣

**Haven - Camberwell**
King's Collage Hospital, Denmark Hill, London SE5
ስልክ፡- 020 3299 1599

**Haven - Paddington**
St Mary's Hospital, Praed Street, London W2
ስልክ፡- 020 7886 1101

**Haven - Whitechapel**
The Royal London Hospital, Whitechapel Road, London E1
ስልክ፡- 020 7247 4787

ቻይልድላየን (ChildLine)፡- የስልክ ቁጥር 0800 1111 ጥሪ ቀንም ሆነ ማታ በማንኛውም ጊዜ ከክፍያ ነፃ ነው። ቻይልድላየን የተበሳጩ ወይም አደጋ ይደርስብናል የሚል ሥጋት ያጋጠማቸው ልጆችና ወጣቶች መርጃ የስልክ መስመር ነው። ስልጠና የተሰጣቸው አዋቂዎች ማፅናኛ፣ ምክርና ከለላ ይሰጣሉ።

ሳማሪታንስ (Samaritans)፡- የስልክ ቁጥር 08457 90 90 90 ቀንም ሆነ ማታ በማንኛውም ጊዜ በከተማ ጥሪ ዋጋ አገልግሎት ይሰጣል። ሳማሪታንስ የሚያስቆጣ ነገር ላጋጠማቸውና በማንኛውም ዕድሜ ላይ ላሉ ሰዎች በሰልክ የምክር አገልግሎት ይሰጣል። በተጨማሪም የሚከተለውን አድራሻ ተጠቅማችሁ ኢ-ሜይል ልትልኩላቸው ትችላላችሁ፡ jo@samaritans.org

ፖሊስ፡- የስልክ ቁጥር 999 ቀንም ሆነ ማታ በማንኛውም ጊዜ ከክፍያ ነፃ ነው። ፖሊስ ወሲባዊ በደል ወይም ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች የሚረዱ ልዩ መኮንኖች አሉት። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የቁንቁ ዕገዛ እንድተገኙ እንዲሁም ሴት መኮንን እንዲያነጋግራችሁ ሊያደርጉ ይችላሉ።

የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማዕከል በዩናይትድ ኪንግደም (The Ethiopian Community Centre in the UK (ECCUK)፡- ይህ የማህበረሰባዊ አገልግሎት ድርጅት ትምህርትን፣ ስደትን፣ መኖሪያ ቤትን፣ ጤናንና የመንግስታዊ ድጋፍ መብትን በተመለከተ ምክርና መረጃ ይሰጣል። ባህላዊ ፕሮግራሞችንም ያዘጋጃል። አድራሻው፡- Selby Centre, Selby Road, London N17 8JN. ስልክ፡- 0208 801 9224። ድህረ-ገጹ፡- www.eccuk.org

| |
|---|
| በምትኖሩበት አከባቢ፣ ማህበረሰባዊ ድርጅት በተለይም የእናንተን ባህል የሚጋራ ቡድን መኖሩን ለማወቅ ከፈለጋችሁ አዋቂዎችን ማለትም እንደ ማህበራዊ ሰራተኛ ጉዳይ ያለ ሃላፊነት የሚሰማውን ሰው መጠየቅ ወይም ኢንተርኔትን ተጠቅሞ መረጃ ማግኘት ይመረጣል። |

አዘጋጆች፡- Maggie Lay & Irena Papadopoulos,
Research Centre for Transcultural Studies in Health, Middlesex University
Charterhouse Building
Archway Campus
10 Highgate Hill
London, N19 5LW
http:/www.mdx.ac.uk/www/rctsh/

የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ማዕከል በዩናይትድ ኪንግደም (ECCUK)
አለም ገብረህይወት ጋር በመተባበር የተጠናቀረ መረጃ።

የገንዘብ ድጋፍ ያደረገው፡- The Big Lottery Fund
አሳታሚ፡- Middlesex University
Bramley Road
London, N14 4YZ

Copyright © Research Centre for Transcultural Studies in Health, Middlesex University & the Ethiopian community Centre in the UK (ECCUK)
July 2007